የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ሐዳር ፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No. 4
ADDIS ABABA 14th November, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፰/፪ሺ፲፫ ዓ.ም

ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፬/፪ሺ፲፫ ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ.............ገጽ ፲፪ሺ፱፻፬

## Content

Proclamation No.1228/2020

State of Emergency Proclamation for the Prevention of Constitution and Constitutional Order No. 4/2020 Ratification Proclamation.........Page 12,904

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፰/፪ሺ፲፫

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፬/፪ሺ፲፫ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፬/፪ሺ፲፫ ጥቅምት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ/ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀ በመሆኑ፤

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ ፺፫/፪/ሀ/ መሠረት በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ስላለበት፤

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ይህንኑ አዋጅ በሙሉ ድምፅ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፺፫/፪/ሀ/ እና ፶፭/፰/ መሠረት የሚከተለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 1228/2020

**THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA COUNCIL OF MINISTERS STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION FOR PREVENTION OF CONSTITUTION AND CONSTITUTIONAL ORDER PROCLAMATION NO. 4/2020, RATIFICATION PROCLAMATION**

WHEREAS, the Council of Ministers has approved on 4th day of November, 2020 a State of Emergency Proclamation No. 4/2020 for the Prevention of Constitution and Constitutional order;

WHEREAS, based on Article 93/2/a/ of the Constitution the state of emergency proclamation decreed by the Council of Ministers shall be presented to the House of Peoples Representatives within forty-eight hours for approval;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives has ratified this Proclamation by total vote at its session held on the 5th day of November, 2020:

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 93/2/a/ and 55/8/ of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፬/፪ሺ፲፫ ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፰/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ስለማፅደቅ**

ጥቅምት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ/ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀውን ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፬/፪ሺ፲፫ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሙሉ ድምፅ አፅድቋል::

**፫. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ**

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

፪/ የመርማሪ ቦርዱ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሲሆን፣ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ከሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ ሆነው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየማሉ::

**፬. የመርማሪ ቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

መርማሪ ቦርዱ፡-

፩/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ያደርጋል፤የታሰሩበትን ምክንያት ይገልፃል፤

፪/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢ-ሰብዓዊ እንዳይሆኑ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤

፫/ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢ-ሰብዓዊ መሆኑን ሲያምንበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሀሳብ ይሰጣል፤

፬/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃዎች ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት የሚፈፅሙትን ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "State of Emergency Proclamation for the Prevention of Constitution and Constitutional Order No. 4/2020 Ratification Proclamation No. 1228/2020."

**2. Ratification of the Proclamation**

The House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified by total vote the State of Emergency Proclamation for the Prevention of Constitution and Constitutional Order No. 4/2020 at its session held on the 5th day of November, 2020.

**3. State of Emergency Inquiry Board**

1/ State of Emergency Inquiry Board is hereby established;

2/ The Inquiry Board shall comprise seven members to be chosen and assigned by the House of Peoples' Representatives from among its members and from legal experts.

**4. Power and Responsibilities of the Inquiry Board**

The Inquiry Board shall:

1/ Make public within one month the names of all individuals arrested on account of the state of emergency together with the reason for their arrest,

2/ Inspect and follow up that no measures taken during the state of emergency are inhuman,

3/ Recommend to the Prime Minister or to the Council of Ministers corrective measures if it finds any case of inhuman treatment,

4/ Ensure the prosecution of perpetrators of inhuman act;

፭/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲቀጥል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

፭. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ወራት የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሕዳር ፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ/ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

5/ Submit its views to the House of People's Representatives on a request to extend the duration of the state of emergency.

5. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of the 4th day of November, 2020 for six months.

**Done at Addis Ababa, on this 14th day of November, 2020.**

**SAHILEWORK ZEWUDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**